
ግንቦት 28/2000 ዓ.ም

## የተወደዳችሁ የግልና የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች
## እንዲሁም ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች

ጥሪያችንን አክብራችሁ በዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ስለተገኛችሁ በእኔና በፓርቲያችን በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ስም አመሰግናለሁ፡፡





በእስሩ ወቅት በደረሰብኝ እንግልት በመታመሜ በውጭ አገር ሕክምና ላይ እንደነበርኩ በሁላችሁም ዘንድ ይታወቃል ብዬ አስባለሁ፡፡ ከሕመሜ እንድድን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገናዊ ምኞቱንና ድጋፉን ከተኛሁበት ሆስፒታል ድረስ በስልክና በተለያዩ መገናኛዎች በመጠቀም ስለገለፀልኝና ስለአበረታታኝ እንዲሁም በያለበት ሆኖ ጸሎት ስላደረገልኝ በእናንተ በኩል ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

### <u>የተወደዳችሁ ወገኖቼ!</u>

እንደ ኢትዮጵያ ኋላ ቀር በሆኑ የአፍሪካ አገሮች እጅግ አስፈሪ የሆኑ ደም አፋሳሽ ችግሮች እየታዩ መሆናቸው ለሁላችንም የተለመደ ክስተት እየሆነ መጥቷል፡፡ ክስተቱን የተላመድነው ቢሆንም ጉዳዩ ግን እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ ሳላነሳው አላልፍም፡፡ በአንድ በኩል የመልካም አስተዳደር መታጣት በሌላ በኩል ደግሞ የኑሮ ውድነት እያሻቀበ መሄድ ሕዝቡን በሕይወት ሊኖር ከማይችልበት ደረጃ ላይ አድርሰውታል፡፡ በአስተዳደሩ ያልተመቸውና ችግር የተበተበው ሕዝብ ደግሞ ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሕዝቡን ሠላምና የሥራ ፍላጐት የሚያዳክመው በመሆኑ ችግሩ እየባሰ እንደሚሄድ ለሁሉም ጉልህ ነው፡፡ ረሀብ፣ ድንቁርናና ድህነት ተባብረው ለደቆሱት ሕዝብ ደግሞ የተስፋ ምንጩን የሚያጨልመው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የእነዚህ ችግሮች ድምር የሕዝቡን መንፈስ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይመራ በክብ ጠረጴዛ ተወያይቶ መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡

ለአገር የሚበጅ ሥራ ለመሥራት መልካም አስተዳደር ያስፈልጋል፡፡ ለመልካም አስተዳደር መሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁንታ ነው፡፡ ስለሆነም ከሁሉም በቅድሚያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጐት ማጤን ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ደግሞ በኢትዮጵያ ምድር የዴሞክራሲ መብቶች ፍትሕና እኩልነት ከሁሉ በፊት ሰፍነው ማየት ነው፡፡ ፍትሕ፣ አንድነትና እኩልነትን ለማስፈን መወያየትና ከውይይቱ ለአገራችን የተረጋጋ አስተዳደር ጠቃሚ የሚሆኑ መሪ ነጥቦችን መያዝና እነዚህን አክብሮ ለመራመድ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

## ውድ ወገኖቼ!

የአገራችን ፖለቲካ በተረጋጋና በሥልጡን መንገድ መካሄድ አለበት፡፡ ይህንን የምንለው የሥልጣኔ መንገድ ለሁላችንም በሚጠቅም ሁኔታ መሰናዳት እንዳለበት ስለምናምን ነው፡፡

በመሠረቱ የሁላችንም የትግል ማዕከል የኢትዮጵያ ሕዝብ በመረጠው መንግሥት እንዲተዳደር ማስቻል ነው፡፡ ትልቁ ችግር ግን ሕዝብ የመረጠውን



መንግሥት እንዴት ያግኝ? የሚለው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለፕሮፓጋንዳ ስልት ተብሎ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት በገዥው ፓርቲ ተዘውትሮ የሚነገረው የመልካም አስተደደር መኖር መሠረቱ ዴሞክራሲ ነው፤ ይህ ዴሞክራሲ እንዴት ይምጣ? የሚለው ጥያቄ ያለፈውን ምርጫ ለመረመረ ሁሉ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መልሱ ቀላል ሊሆን አልቻለም፡፡ የመልካም አስተዳደር መሠረት የሆነው ዴሞክራሲ ሥርዓት በእውነተኛ ድርጊት እንጂ በቃላት ድርደራ ሊመጣ ወይም እንደሚነገረው ሆኖ አለመገኘቱን በተግባር አይተናል፡፡ ከጥቃቅን የአስተዳደራዊ ሥራ ጀምሮ የዴሞክራሲ ሥርዓት ዋስትናው በገዢው ፓርቲ የሚነገሩ ቃላት እንዳልሆኑ ሁላችንም በተግባር ያየነው ጉዳይ ነው፤ ዴሞክራሲ ከተመቻቹና ከጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅቶች ሕልውና ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ጠንካራ የሠራተኛ ማኅበር፣ የመምህራን ማኅበር የኗሪዎች ማኅበራት እና የመሳሰሉት እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ እነዚህ እንዲኖሩ ለማድረግ ደግሞ ለዴሞክራሲ መኖር ቆርጦ የተነሳ መንግሥት መኖር የግድ ነው፡፡ እኛ ችግራችንና የበለጠ

የሚያሳስበን እነዚህን ማጣታችን ብቻ አይደለም፤ ለምንጊዜው እንዳይኖሩ ደብዛቸው የሚጠፋበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑ እንጂ፡፡ ለዚህ ነው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የዴሞክራሲ ሥርዓት በአስተማማኝ ሁኔታ በአገራችን ሊኖር የሚችልበትን መሠረት የሚሆኑ ጥያቄዎች ያቀረበው ዛሬም ለሁላችን የሚጠቅም ሥራ እንዲጀመር መጠየቅ ግዴታችን ነው፡፡ ስለሆነም ዛሬም ነፃ የምርጫ ቦርድ እንዲኖር እንጠይቃለን፡፡ በሕዝብ የበላይነት የምናምን ከሆነ የሕዝብ የበላይነት የሚረጋገጠው በነፃ ምርጫ መሆኑን የሁላችንም እምነት መሆን አለበት፡፡ ነፃ ተወዳዳሪዎች ካሉ ደግሞ ከሁሉም ነፃ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ መኖር የግድ ይሆናል፡፡

ዴሞክራሲ በአገራችን እንዲሰፍን ዛሬም የፍትሕ አካላት በእውነትና በእኩልነት ሕዝብን ያገልግሉ ብለን እንጠይቃለን፡፡

ዛሬም የፖሊስና የደህንነት ተቋማት ነፃ የሕዝብ አገልጋይ ይሁኑ እንላለን፡፡

ዛሬም መገናኛ ብዙሀን የሙያው ሥነ ምግባር በሚፈቅደው መንገድ በነፃነት ይሥሩ እንላለን፡፡

ዛሬም የሕዝቡ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመሳሰሉት መብቶቹ ይከበሩለት ብለን አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

## ክቡራትና ክቡራን ወገኖቼ!

በነዚህ ሕዝባዊ ጥያቄዎቻችን ምክንያት ማናቸውንም እንግልቶች ሁሉ ተቀብለናል፡፡ ለአገርና ለሕዝብ ጉዳይ ስንል የደረሱብን በመሆናቸው ቂም አንይዝም፡፡ በቂም በቀል አገር እንደማይገነባ እንገነዘባለንና ሁልጊዜም ትግላችንን በፍቅር እናካሂዳለን፡፡ በአገራችን ያለውን የምርጫ ሥርዓትና አፈፃፀም እንዲስተካከል የምንታገለው በአንድ ወቅት ገዢ የሆነ በድምፅ ምርጫ ከሥልጣን ወርዶ ተቃዋሚ የሚሆን ከሆነ ለሱም የሚጠቅም ሕግ መኖር ለሁላችንም ጠቃሚ መሆኑን በማሰብ ጭምር ነው፡፡ ይህን ያልተቀበለና ከሕዝብ ጥያቄ ጋር እልህ መግባት ወደ ገደል የሚያደርስ መንገድ መከተል መሆኑን ደጋግመን መክረናል፤ በእርግጥም ተቃዋሚን ለማጥፋት ወይም ለማዳከም በተደረገው ሙከራ ብዙዎቻችን መስዋዕትነት ከፍለንበታል፤ በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገደብ የሌለው መስዋዕትነት ከፍሎበታል፤ ከዚህ መስዋዕትነት በኋላ በዚሁ መንገድ ልቀጥል የሚል ወገን ይኖር ይሆን? የሚል ጥያቄ ዛሬ ላይ ሆኖ ማቅረብ ምናልባት የዋህነት ሊመስል ይችላል፤ እኔ ግን ዛሬም

ይህን ጥያቄ አነሳለሁ፤ የምጨምረው ሌላ ጥያቄ ቢኖር እስከመቼ በዚህ ሁኔታ እንቀጥላለን? የሚል ነው፡፡

ገዢና ተገዢ ተፋጠውና እልህ ተያይዘው፣ በልማት ጐዳና ለመራመድ በፍፁም አይቻልም፤ ምናልባትም ለዚህ መፋጠጥ ምክንያት ለመስጠት ሞክረንም ከሆነ ይህ ለስንት ጊዜ ሊያገለግለን እንደሚችል መገመት ይጠበቅብናል፡፡ በአጠቃላይም ድህነታችን ያመጣብን ችግር ነው ብለን ብንናገር ከንቱ መግደርደር ይሆናል፡፡ ድህነትንም ቢሆን ለማሸነፍ ፍሬ ነገሩና ትኩረት መደረግ ያለበት በጋራ ተሰልፈን እጅ ለእጅ ተያይዘን በሕግና በሕዝብ የበላይነት ላይ ተማምነን ወደ ልማት ሥራችን መሰማራት ላይ ነው፡፡ ማንኛውም ወገን በሥልጣን ላይ የሚያቆየውን የምርጫ ሥርዓትና የምርጫ አስፈጻሚ አካል በማቋቋም የሕዝብን ራዕይ ለማጨለም ቢሞክር ይህ መንገድ የሚያስከትለው ውድቀት የችግሩ ፈጣሪ አካል እዳ መሆኑን መረዳት ይጠቅማል፡፡ ይህን መንገድ ተቃውሞ የብረት ክንዱን በጥያቄዎቻችን ላይ ለመጫን የሚሞክር ቢኖር ኃላፊነቱን በግሉ መሸከም ይኖርበታል፡፡ አገሪቱ ለሚደርስባትም ችግር ተጠያቂ መሆኑንም ሊገነዘብ ይገባል፡፡

ዓለም ጠባብ መንደር ሆናለች፡፡ በዚህም ድህነታችንና መንስኤውን በዓይናችን እያየን ነው፡፡ ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተፈፀመውን ምርጫና ከምርጫ ጋር ተከታትሎ የመጣውን ችግር የዓለም ሕዝብ በዓይኑ አይቷል፡፡ ትላንት የኬንያን ምርጫ ተከትሎ የተካሄደውን እልቂትም ተመልክተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች አንገት ለነበረው የኬንያ ምርጫ የሰጡትን መፍትሔ አድምጠናል፤ ታዝበናልም፡፡ ሁኔታው ኢትዮጵያውያንን አስታዋሽ ያጣን ብቸኛ ሊያስመስለን ይችል ይሆናል፡፡ ለምን የኛ ጉዳይ ዝም ተባለ? የሚል ጉርምርምታ እያስከተለም ይሆናል፤ የእኛ ጉዳይ ጉዳያቸው ሆኖ ምንም ባያሳስባቸውም እኛ ኢትዮጵያውያን ግን በራሳችን የምንተማመንና ለችግሮቻችን ሁሉ ራሳችን መፍትሔ ስንሰጥ የቆየን ነንና ዛሬም ለችግራችን መፍትሔ መስጠት እንችላለን የሚል እምነት ያለን ነን፡፡ እዚህ ላይ ትልቁ ነጥብ ሕዝብ ለውጥ ይፈልጋል፤ ይህ ለውጥ በሕዝብ ነፃ ምርጫ መምጣት እንዳለበት እንጂ መንግሥት ችሮታ የሚሰጠን አይደለም፡፡

እርስ በርስ በመገዳደል፣ ወይም በማሰር ለችግሩ መፍትሔ ሊመጣ እንደማይችል አይተናል፡፡ እኛ እየገደሉን፣ እያሰሩን፣ እያንገላቱን ከሥራ እያባረሩን፣ እያስራቡንና፣ ከዚህም የበለጠ እየፈጸሙብንም ቢሆን ቀበቷችንን ጠብቅ አድርገን ሰላማዊ ትግላችንን

ለመቀጠል ወስነናል፡፡ ይህን የምናደርገው ለዘላቂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ስንል ብቻ ነው፡፡

ለዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታ እስከዛሬ በአገራችን የተደረጉት ትግሎች አብዛኛውን ጊዜ የጉልበት መንገዶች ነበሩ፡፡ በጉልበት ሥልጣን የያዘው በሌላው ጉልበተኛ ሲፈነቀል ዘመናት በከንቱ አለፉብን፡፡ እስቲ በሕዝብ ፈቃድ እንጓዝ ብለን ስንነሳ በሃሰት ወንጅለው አሰሩን፤ እስከ እድሜ ልክ ፈረዱብን፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ ዛሬም ቢሆን እኛ የመረጥነው ብሩህ የሕዝብና የአገር ግንባታ መንገድ የሆነውን ሕዝብ በነፃ ምርጫ የራሱን መንግሥት የሚያቋቁምበትን ሠላማዊ መንገድ መከተል ብቻ ነው፡፡ ይህ መንገድ ረጅምና ለጥቃት የሚያጋልጥ እንደሆነ እናውቃለን፤ ዘላቂውና አስተማማኙ የለውጥ መንገድ ይኸው ብቻ ስለሆነ ግን እንገፋበታለን፡፡ አንዳንድ ሰዎች በመሳሪያ ኃይል አሸንፎ ሥልጣን የመያዝ መንገድ ቀላል እንደሆነ አድርገው ያስቡ ይሆናል፤ ይህ መፍትሔ እንዳልሆነም ያለፉትን ሂደቶች ከአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ መረዳት ይቻላል፡፡ አምባገነን አንስቶ ሌላ አምባገነን ማንገሥ ነውና ፋይዳ የለውም፡፡

ሕዝብ የመረጠው ሥልጣን መያዝ እንዳለበት የእኛ ብቻ ሳንሆን የገዢዎቻችንም እምነት ሊሆን ይገባል፡፡ ጨዋታው ያለው ምርጫ ከሚለው ላይ ነው፡፡ በምርጫ ስም ገዢዎች የአገዛዝ ዘመናቸውን የሚያራዝሙበት ስልት አሳሳቢ ነው፡፡ መወያየትና መተማመን ያለብን ምርጫ እንዴት? በሚለው ላይ መሆን ይኖርበታል በምንም ምክንያት ቢሆን ለተረጋጋ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማታለያ የሌለው ነው፡፡ የገዢዎቻችን ጨዋታ ትኩረት የሚያደርገው ምርጫን እንዳይኖር በማድረግ ላይ ሳይሆን የማስመሰያ ምርጫ በማካሄድ የሕዝብን እምነትና ፍላጐት ማዳከም የሚችልበትን ስልት ከመቀየሱ ላይ ነው፡፡ በአገራችን እውነተኛ ምርጫ እንዲኖርና የሕዝብ ፈቃድ እንዲፈፀም የምንታገለው ለዚህ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት በምንም መልኩ ይምጣ ማረጋገጫው ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት መኖርና መፈፀሙን ማረጋገጥ ነው፡፡ ዴሞክራሲ በሌለበት አገር ስለ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መናገርን እንደ ፕሮፓጋንዳ የሚቆጥሩ ወገኖች እንዳሉ እገነዘባለሁ፡፡ እኔ ስለ ምርጫ ጥሩነት የምናገረው በተደላደለ ፍራሽ ላይ ሆኜ እንዳልሆነ ትረዱኛላችሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ ለሰላማዊ ትግል ያለን እምነት በየምክንያቱ እንዳይንሸራሸር በእጅጉ መጠንቀቅ እንዳለብን አምናለሁ፡፡ ችግሮቹ ምንም ያህል ውስብስበና አሰልቺ ቢሆኑም በትዕግስት የመረጥነውን መንገድ መከተል ይኖርብናል፡፡

ትዕግስታችን እንዲያልቅ በራሳችን ፓርቲ ውስጥም መከፋፈልን እየፈጠሩ ጽናታችንንና ዓላማችንን የበለጠ እየፈተኑት መሆኑን ታውቃላችሁ። ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የተለያዩ ጊዜያዊ ችግሮች እያጋጠሙት ይገኛል። ችግሮቻችንም በውጭም በውስጥም ኃይሎች የሚቆሰቆሱ ተልዕኮአቸውም የሕዘብ ልጅ የሆነውን ቅንጅትን ማዳከም ብቻ ሣይሆን ማፈራረስም ነው። ይኸውም ሕዝብ የሞተለትንና የ1997 ምርጫ ዋነኛ ተዋናይ የሆነውን ቅንጅት የሚለውን ፓርቲ ዋጋ ማሳጣት ነው፤ ለዚህ የመጀመሪያው ማዳከሚያ መንገድ ቅንጅት የሚለውን ስም ለሌላ አካል፣ የምርጫ ምልክቱንም እንደዚሁ ለሌላ ቡድን የመስጠት እርምጃ መውሰድ ነው።

ከዚያ የቀጠለው ትልቅ የሕዝብ እምነትና አደራ የተጣለበትን የቅንጅት አመራር በሰርጎ ገቦች ተንኰል እንዲበታተን ማድረግ ነው። ይህም ተጀምሮ ከሥራ ላይ እየዋለ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የፓርቲዎች መብዛት የሚያስደስተው ይመስል ፓርቲያችንን በውጫዊና በውስጣዊ ጫና እየሰነጣጠቁ የተወሰኑ ግለሰቦች ከመካከላችን እያወጡ ትናንሽ ፓርቲዎችን እንደ ችግኝ በማፍላት ሙከራ ላይ ይገኛሉ። ይህ ድርጊት ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን እንደማያፈርሰውና የሕዝቡን የዴሞክራሲ ጥያቄ እንደማያዳክመው እንዲገነዘቡ እመክራለሁ። ሕዝቡ ራሱ መስታወት ነው፤ ከቅንጅት የወጡ አፈንጋጮች ለማን እንደቆሙ ለምን መበታተን እንደመረጡ ይረዳል። ስለሆነም እውነተኛውንና ቁርጠኛውን አመራር ተከትሎ በሰላማዊ ትግሉ ይገፋበታል።

በቅንጅት መንፈስና በሕዝብ ፍላጐትና መንገድ ለመጓዝ ቆርጠን የተነሳነውን ተስፋ ቆርጠን እንድንበታተን ማድረግም ፓርቲያችንን ለማዳከም የመረጡት ሌላው መንገድ ነው። የሕዝብን ጥያቄና ፍላጐት የሚያራምድ ፓርቲ እስካለ ድረስ የሕዝብ ጉዳይ ተዳፍኖ እንደማይቀር በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። ይልቁንም በሞቀ የሕዝብ ትግል ወቅት የመከፋፈል ሥራ በሚሠሩት ላይ ሕዝብ እንደሚያዝን ፓርቲያችንን ሊከፋፍሉ የተነሱ ግለሰቦች ሊገነዘቡ ይገባል። እኩይ ተግባራቸውን ዘመንና ታሪክ አይረሳውምና።

በእኛ በኩል ግን ትልቁ ተስፋችንና የብረት ጋሻችን የሆነው ድረስልን ስንለው የሚደርስልን፣ ምርጫ ወጥተህ ምረጥ ስንለው ከንጋት እስከ ምሽት ከቤቱ ወጥቶ ሳይሰለች ለምርጫ የሚቆምልን፣ ተሰብሰብ ስንለው የሚሰበሰብልን፣ ሰልፍ ውጣ ስንለው የሚሰለፍልን ታላቅ ሕዝባችን ስለሆነ እሱን መከታ አድርገን በዓላማችን ፀንተን አሁንም የቆምን መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስጋና ይግባውና

ዛሬም ከኛ ጋር የቆመ መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጾልናል፡፡ ሕዝብ በኛ ላይ ተስፋ እንደጣለብን ሁሉ እኛም የሕዝብን ተስፋ በማክበር በቆራጥነት እየተንቀሳቀስን እንደሆነ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ፡፡ በመሆኑም በአዲስ መንፈስ ተነስተን የፓርቲያችንን ሥራ የምናከናውነው እስከመጨረሻው ቀበሌ ድረስ መዋቅራችንን የምንዘረጋበትን ሁኔታ በማፋጠን ነው፡፡

ዛሬ እኛን ግራ የሚያጋባን ከመካከላችን ወጥተው የራሳቸውን ፓርቲ ያቋቋሙ ግለሰቦች እንቅስቃሴ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ማቋቋሚያ አዋጅ በሚፈቅደው ሁኔታ ሕግን መከታ አድርገን የምንከተለውንና የምናካሂደውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሥልጣንን ጋሻ አድርገው ሊያጠቁን የሚነሱ ወገኖች ተግባር እንጂ፡፡ እነዚህን አካላት ስለ ሕግና ስለ ኢትዮጵያ አምላክ ብለው ሕግን እንዲያከብሩ እንጠይቃቸዋለን፡፡ ጊዜ ይወስድ እንደሆነ እንጂ የአገርንና የሕዝብ ጉዳይ አድማጭ የሚያገኝበት ጊዜ ሩቅ እንዳልሆነ እምነታችን ነው፡፡

ምስጋና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ለቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባላት ይሁንና የሕዝብ ፓርቲ የሆነውን ቅንጅትን ከማንኛውም ጥቃት ለመከላከል አባላት ንቁ ተሳትፎ አሳይተዋል፡፡ ቅንጅት ዛሬም የሚሊዮኖችን አባላት ምርኩዝ ይዞ፣ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ ተላብሶ ሰላማዊ ትግሉን ይቀጥላል፡፡ ይህም በመሆኑ በሕግ ስም ቅንጅት የሚለው መጠሪያ ለሌላ ፓርቲ ቢሰጥም ፓርቲያችን ትግሉን አያቋርጥም፤ ከሕዝቡ ያገኘውን የቅንጅት መንፈስ እንደያዘ በጠንካራ ፓርቲነት በሰላማዊ ትግሉ ወደፊት ይጓዛል፡፡

አፈንጋጮች ‹‹በየፊናችን እንጓዝ፣ እንለያይ›› እያሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይሰብኩ የበረውን መርህ ዓለምንም ውይይት ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ የሊበራል ዴሞክራሲ መርህ የሚያራምደው ፓርቲያችን የሃሳብ ልዩነቶችን የሚያስተናግድና በውይይት መፍትሔዎችን ማምጣት የሚችል መሆኑ በቅንጅት አመራር አባላቱ ዘንድ እየታወቀ አፈንጋጭ ግለሰቦች ግን ምንም ዓይነት የውይይትና የመፍትሔ ፍለጋ መንገዶችን ሳይጠቀሙ ፓርቲያቸውን ጥለው አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም ወስነው ሥራቸውን ጀምረዋል፡፡

በእስር ቤት የነበረው የቅንጅት አመራር ከእስር እንደወጣ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ የወሰነው በዚያ የሚገኙ የፓርቲውን ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ለማጠናከርና በየጊዜው ስለሚያደርጉልንም ማበረታታት ለማመስገን ነበር፤ ነገር ግን ቅንጅትን ለማፈራረስ የቤት ሥራ ይዘው ወደ ፓርቲው የመጡ ግለሰቦች በመገንባት ፈንታ

አንድነትን መናድ ዓላማቸው ስለነበር በውጭ በቆዩባቸው ጊዜያት ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን እየከፋፈሉ በማዳከም የራሳቸውን ተለጣፊ ድርጅቶች ሲያቋቁሙ ቆይተዋል፡፡ በዚህ ድርጊታቸውም ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መስፈን ሌት ከቀን ሲጮህ የነበረውን በውጭ ኗሪ የሆነውን ዜጋችንን ልብ አቁስለዋል፡፡

በውጭ አገር የሚገኙ የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶቻችንን እንደነበረ ለመመለስ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም በውጭ ቆይታዬ የተበታተነውን ለማሰባሰብና ሃቁን ለማስረዳት ከሌሎች የትግል ጓደቼ ጋር ባደረግነው ጥረት በውጭ ያለው የድጋፍ ኃይላችንን አንድነት መልሶ እንዲገነባ አድርገናል፡፡

ተገንጣዮቹ ወደ አገር ቤት ከተመለሱም በኋላ ቢሆን የመከፋፈሉን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ቀጥለውበታል፡፡ በዚህም የቅንጅትን ነባሩን ቢሮ ረግጠው በመውጣት፣ በጽ/ቤቱም አካባቢ ተራ አምባጓሮ እስከመፍጠር ደርሰዋል፡፡ ከዚህም በቀጠለ በእውነተኛና በጠንካራ የቅንጅት አመራር አባላት መልካም ስም ላይ ውዥንብር የሚፈጥሩ ጽሑፎችን በመገናኛ ብዙኃን በመበተን ፓርቲው መሠረት እንዲያጣ ሞክረዋል፡፡ እነዚህንና ሌሎችን የፓርቲውን አንድነት የሚያናጉ በርካታ እንቅስቃሴዎች አከናውነዋል፡፡ የአፈንጋጮቹ መጥፎ ሃሳብና ድርጊት በጠንካራ አመራሮች፣ አደራጆች፣ አባላትና ደጋፊዎች ያላሰለሰ ጥረት ሊመክን ችሏል፡፡ ይህ እኩይ ድርጊታቸው ከእንግዲህ ወዲያም ቢሆን ፋይዳ አይኖረውም፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በአሁን ወቅት ሙሉ በሙሉ ከእኛ ተነጥለው ሌላ ፓርቲ ለማቋቋም ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በምንከተለው የሊበራል ዴሞክራሲ መርሕ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እምነቱን በፈለገው ፓርቲ ውስጥ ተሰልፎ እንዲያራምድ ስለሆነ ከቅንጅት ፓርቲ ተለይተው የራሳቸውን ፓርቲ ለማቋቋም የወሰኑትንም ሰዎች እርምጃ እናከብራለን፡፡ በመከባበር የሰለጠነ ፖለቲካ የምናራምድ በመሆኑ ውሳኔያቸውን አንጋፋም፡፡

በእኛ በኩል ከእንግዲህ ትኩረት ሰጥተን የምንቀሳቀሰው የፓርቲያችንን መዋቅር እስከመጨረሻው ቀበሌ በመዘርጋትና የፓርቲውን ውስጣዊ ጥንካሬ በመገንባት ይሆናል፡፡ እስካሁንም ከእስር ከተፈታን በኋላ ባሉት ጊዜያት በዋናው ጽሕፈት ቤታችን አስተባባሪነት

## ከእስር ቤት መልስ ባሉት ጊዜያት ከአዲስ አበባ ውጭ

- በተከታታይ የመስክ ጉዞዎች አብዛኛውን የኢትዮጵያ ክፍል ዳሰናል፡፡
- ከሃያ በላይ የሚሆኑ ቢሮዎችን ከፍተናል፡፡
- ቢሮ ባልከፈትንባቸው አካባቢዎች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች አዋቅረናል፡፡

- የተበታተኑ አባላትን አሰባስበናል፡፡

**በአዲስ አበባ ውስጥም**

- በአስሩም ክፍለ ከተሞች መዋቅራችንን ዘርግተናል፡፡
- የሴቶችና የወጣቶችን ኮሚቴዎች አዋቅረናል፡፡
- የአባላትን የፖለቲካ ግንዛቤ ለማዳበር ተከታታይ የመማር ማስተማር ሂደት በቀጣይነት እንዲካሄድ አድርገናል፡፡
- ለተደጋጋሚ ጊዜያት በአገር ውስጥና በውጭ በሚገኙ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የፓርቲያችንን እንቅስቃሴ አስተዋውቀናል፡፡
- በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ ላሉ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን የፖለቲካ ግንዛቤ ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ ጽሑፎችንና የሚደመጡ መልዕክቶችን አሰራጭተናል፡፡ በውጭ አገር በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓ፣ በደቡብ አፍሪካና በአውስትራሊያ ከሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶቻችንና በአሜሪካ ካለው የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት ጋር የሥራ ግንኙነት አድርገናል፡፡

እነዚህንና ሌሎች ጅምር እንቅስቃሴዎቻችንን ወደፊትም የበለጠ አጠናክረን ከሕዝባችን ጋር በመሆን በስፋትና በጥልቀት የምንንዝባቸው ይሆናል፡፡ ቀድሞ የነበረንንም ብርቱ የትግል መንፈስ ተላብሰን በበለጠ ጥንካሬ ሰላማዊ ትግላችንን እንደምንቀጥልበት በድጋሚ አረጋግጣለሁ፡፡

የቅንጅት ስም፣ አርማና የምርጫ መወዳደሪያ ምልክት አላግባብ ለሌሎች መስጠቱን በመቃወም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ስላቀረብን ፍትሕ እናገኛለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ከእስር ቤት ስንፈታ ከኢሕአዴግ ጋር ድርድር እንደሚጀመር በሽማግሌዎች ተገብቶልን የነበረው ቃል ተግባራዊ ባለመሆኑ ትኩረት እንዲሰጠው የሚመለከታቸውን በዚህ አጋጣሚ ለመጠየቅ እሻለሁ፡፡

በመጨረሻም በሌላ ፓርቲ ውስጥ ያልገቡ ወይም አዲስ ፓርቲ ለመመስረት ያልተንቀሳቀሱ እራሳቸውን አግለለው የተቀመጡ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትና ሌሎችም የፓርቲው አባላት ወደ ቅንጅት ፓርቲ በመምጣት ጀምረውት የነበረውን ትግል እንዲቀጥሉ እጋብዛለሁ፡፡

ማብራሪያ በሚፈልጉ የፓርቲው ጉዳዮች ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

**ቅንጅት አንድ ነው!!**

**ኢትዮጵያም አንድ ናት**

**ኃይሉ ሻውል**

**የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ**

**ፓርቲ ሊቀመንበር**